# ለመሆኑ ኢትዮጵያ አሁን አገር ናት ወይ?

*በላይነህ አባተ* abatebelai@yahoo.com *የካቲት ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*

ይህችን ጽሑፍ ለማሰናዳት በማሰብና በማሰላሰል ላይ እያለሁ አቶ አበበ ገላው እንደኔ እንደኔ ሁሉም ጦቢያዊ መጠየቅ አለበት ብዬ የማምነውን ጥያቄ እንዲህ ብሎ ጠየቀ። *"ኢትዮጵያ የማን አገር ናት?"* [1] ጥያቄውን በጥያቄ መመልስ ሆነብኝ እንጂ የኔ መልስ "ለመሆኑ ኢትዮጵያ አሁን አገር ናት ወይ?" የሚል ነው። ሰው ያለውን ከአካፈለ ንፉግ አይባልምና ይህንን ያልኩበትን ምክንያት ለመግለጽ ስለምሞክር "ወገኛ ዛሬም አያልቅበት ወጉን ይጠርቃል!" እያላችሁም ቢህን በትእግስት ተከታተሉኝ። ወትሮም ቁም ነገርም ቢሆን ሲጫወቱት የሚያምረው እንደዚህ እያለ ልክ ልክን የሚነግር ተራቢ ከመካከል ሲኖር ነው።

እንደ ውዳሴ ማርያም ቃል በቃል አልወጣሃውም ብላችሁ ከመሪጌታ ውቃው ዜማ እንደሚቀበል ዲያቆን ወዝ በጠጣ መቋሚያ ደልዛችሁ ከቤተ-መቅደስ አታስወጡኝ እንጅ አባታችን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም አገር ምን እንደሆነ በተለያዩ አጋጣሚ ሲያስተምሩ እንዲህ ብለው ነበር። "አገር ከዚህ ቀደም የነበረውን፣ አሁንም ያለውን፣ ወደፊትም እስከ ፍጻሜው የሚመጣውን ትውልድ የሚያጠቃል ጽንሰ-ሐሳብ ነው።" [2] ከዚህ የጠለቀ፣ ያማረና የተዋበ ሌላ አገላለጥ ይኖራል ብዬ ስላልገመትኩ የርሳቸውን ትርጉም እንደወረደ ተቀብየዋለሁና እናንተም ለጊዜውም ቢሆን ይህችን ልብ ብላችሁ ያዙልኝ። የአገር ትርጉሙ ይህ ሆኖ ሳለ ለቅጣት አምላክን በጽኑ ከሚቃረነው ሐይል የተላኩ በሚመስሉ ከንቱ መልእክተኞች የበፊቱ የጦቢያ ትውልድ ሙልጭ ተደርጎ ተክዷል። የአሁኑ ትውልድም ጓያ እንደሰበረው ተቀፍድዶ ጉልበትና ጉልበቱን እርስ በርሱ እያማታ እንዲሽመደመድ ተገዷል። "ስልፈሰፈስ ከመኖር አንድ ቀን ቀጥ ብየ ሄጀ የመጣው ይምጣ!" ብሎ የቆረጠውንም ቀና ሲል ካለ ርህራሄ እንደ ዳንግሌ ጠቦት ይሰውታል። የወደፊቱ ትውልድም የባህር በሩ ብቻ ሳይሆን ሌላ ሌላውም እድሉ ተዘግቶበት ገና ብዙ መከራና ፈተና ይጠብቀዋል። እንግዲህ ከቀደመው፣ ከአሁኑ ወይም ከወደፊቱ አንዱንም ያልያዘችው ጦቢያ አገርነቷ ከምኑ ላይ ነው?

እኔ በበኩሌ አገርን የማይበት ሌላም መነጽር አለ። ልብ ብላችሁ ከሆነ አበሻ "አስራ ሁለት አካላቴን" የሚለው ነገር አለው። የሥነ-ህይወት ጥናት (ባዮሎጅ) እንደዚሁ አስራ ሁለት የአካል ሰንሰለቶች (body systems) አሉ ይላል። [3] ይህንን ያጤነ አንዳንዱ አበሻ የሥነ-ህይወትን ሳይንስን የጀመረው አበሻ ነው ብሎ መጀነን ይቃጣዋል ብዬ እገምታለሁ። ምክንያቱም አንዱን ትቶ አንዱን ሆነብኝ እንጅ ፈረንጅን ቁምጣ ለብሶ ያዩ ቆፍጣና ጦቢያውያን "ቁምጣ መልበስ ለአለም ያስተማርን እኛ ነን!" እያሉ ሲንቦጣረሩ በአይኔ በብረቷ አስተውያለሁና። ወደ ቁምነገሩ እንመለስና አስራ ሁለት የሰውነት ክፍል ሰንሰለቶች የሚባሉትም የነርቭ፣ የደም ውህደት፣ የእስተንፋስ፣ የምግብ መፍጫ፣ የሽንት፣ የዘር ስሪት፣ የአጥንት፣ የመገጣጠሚያ፣ የጡንቻ፣ የቆዳ/ጥፍር/ጸጉር፣ የሆርሞንና ሊንፋቲክና የመሳሰሉት ናቸው። እዎ አገርን የማየው እንደ አስራ ሁለቱ የሰውነት ክፍሎች በጥብቅ ተሳስሮ አንድ ሆኖ መከራውንም ደስታውንም የሚጋራ የሰዎች፣ የእንስሳት፣ የአትክልትና ግዑዝ ነገሮች ጥምረት ሆኖ ነው። እነዚህ ሁሉ የአካል ሰንሰለቶች በአንድ ቆዳ ተለብደው በፍቅርና በጤና እየኖሩ ሰውን ሰው አድርገው እንደሚያኖሩት ሁሉ ሐገርንም ሕዝቡ፣ ለማዳና ለማዳ ያልሆኑ እንሰሳት፣ አትክልት፣ ምድሩ፣ ውሃውና አየሩ አንድ ሰማይ ተጋርተው በመተጋገዝ በፍቅርና በሰላም ሲኖሩ አገርን አገር ያሰኙታል። የአንድ የአካል ክፍል ሲናወጥ ሌላው በጤና እንደማያድር ሁሉ የደን መጥፋት ሕዝቡን፣ እንሰሳው፣ መሬቱን ወዘተ ሁሉ ጤና ይነሳዋል። እንደ ተፈጥሮና ማህበራዊ ሕግ ከሆነ ጣት ላይ ያለ የነርቭ ጫፍ በተጎዳ ቁጥር ሕመሙ ራስ ላይ የሚሰማውን ያህል የአገር ሕዝብ አንዱ ክፍል ሲጎዳ ሁሉንም ሕዝብ ይቆጠቁጠዋል።

እንደ አለመታደል ዛሬ በጦቢያ የተዘረጋው ድንጋጌ ግን ሰውና አውሬው ተለማምደው በሰላም አብረው በመቻቻል እየተረዳዱ እንዲኖሩ የሚረዳ ሳይሆን ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ መርጠው ወደዚህ አለም ባልመጡበት ዘር፣ ቋንቋና ጎጥ ተከፋፍለው እየተናከሱ እንዲኖሩ የሚያስገድድ ነው። ይህም ብቻ አይደለም ከዚህ ኢሕብረተሰባዊ ከሆነ መርህ በመነጨ ደንብ ባልና ሚስት ተለያይተው እንዲኖሩ ተገደው ልጆች በመካከል ከአለአሳዳጊ የቀሩበት ጊዜ ነበር፤ አሁንም ይኖራል። በጎሳ ግጭቶች ስንት ሰላማዊ ሰው ህይወቱን አጥቷል፤ በማጣትም ላይ ይገኛል። ታዲያ ነብርና ፍየል አብረው በሰላም በሚኖሩበት በሃያ-አንደኛው ክፍለ ዘመን፣ ክፍለ-አለማት በቴክኖሎጂ ድልድይነት የእልፍኝና አዳራሽ ያህል በተቀራረቡበት ዘመን፣ ሰዎች በቋንቋና በጎጥ ጉረኖ ውስጥ እንደ ጋማ እንሰሳ ታስረው፣ ተቀይደው፣ ወይም ተለጉመው እንዲውሉ ደንብ የወጣበት ምድር አገር ይባላል ወይ? ይህ ጉረኖ ይፍረስ ብሎ የጮኸ፣ ቅይዱ ይፈታ ብሎ የተናገረ፣ ልጓሙ ይውለቅ ብሎ

የጠየቀ፣ ለፍቅር የዘፈነ፣ ለአንድነት የዘመረ፣ ስለ ፍትህ የሰበከና ቃሉን የሰጠ ሰቆቃን በቁሙ የሚጨልጥበት መሬት በእውነት አገር ነወይ?

ኅበዝና ወይዛዝርት ጉዳችን በደረቁ ተዘርዝሮ አያልቅምና ከደከማችሁ ቡናችሁን ፉት አርጉ አለዚያም እንደ መምሬ ቀረ-በከንቱ ዋንጫችሁን ጨብጡ። በህክምና አለም የጤናን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያመለክቱ ዋና ዋና ምልክቶች (vital signs) የሚባሉ እንደ ደም ግፊት፣ ልብ ትርታ፣ የአተነፋፈስ ፍጥነትና  እንደዚሁም የሰውነት ሙቀት ልክ የሚባሉ ምልክቶች አሉ። እነዚህ ተቃውሰው የተገኙ እንደሆን መንስኤውን ለማወቅ ጠለቅ ያለ ምርመራ ይደረጋል። እንደዚሁም የአንድ አገርን የጤና ሁኔታ የሚያመለክቱ እንደ የመወለድ፣ የመሞት፣ የጋብቻ፤ የፍች፣ የጽንስና የህጻናት ሞት መጠን ወዘተ የሚባሉ ዋና ዋና የሕብረተሰብ ጤንነትና እድገት ምልክቶች (vital stastics) ትርጉሙን አሟልተው አገር በሆኑት አገሮች አሉ። [4] እነዚህን ቀመሮች መስራት የሚቻለው ደግሞ ሕዝብ በትክክል ሲቆጠር፣ የልደትና የሞት መዝገብ ሲኖር፣ የሞት ምክንያቶች ሲታወቁ ወዘተ ነው። ጦቢያን ያለ ኮርቻ የሚጋልቧት ጉዶች ግን እንኳን የእነዚህን ጠቀሜታ ሊያውቁ እንደዚህ የሚባሉ ነገሮች መኖራቸውንም የነገራቸው ያለ አይመስልም። ታዲያ ለእንደነዚህ አይነት የጤንነትና የእደገት አቅጣጫ መለኪያ መንገዶች የስራ ማስኬጃ በጀት ከመመደብ ይልቅ እየገበረ የሚቀልባቸውን ለፍቶ አዳሪ ሕዝብ መግደያ ጥይት የሚገዙ፣ ከህጻን እስከ አዛውንት የሚያጉሩበት ወህኒ-ቤት የሚሰሩ፤ እንደዚሁም ሕዝቡ የእውቀት ጭላንጭል የሚያገኝባቸውን እንደ ሬዲዎና ኢንተርኔት ያሉ መገናኛዎችን ለማፈን ብትቶ ከቻይና ሲገዙ የሚውሉ ከንቱዎች የሚረግጡት መሬት አገር ይባላል ወይ?

ከዚህ በፊት በሌላ ጽሑፍ [5] ለመግለጥ እንደሞከርኩት እንደመስታዎት ፊትን ከሚያሳይ ጠረጴዛ ላይ ጠማማ ኮቢያቸውን ብድግ አርገው የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲሻቸው ሰባ አለዚያም ሰማንያ ሺህ እያሉ የፈጠራ ቁጥር እያስቀመጡ እነሱ ዋሽተው አለምን ያስዋሻሉ። የልደት ካርድ ሳይኖር የእድሜ ስታስቲክስ ያወጣሉ። የሞት መዝገብ ሳይኖር የሞት ስሌት ያስቀምጣሉ። ቆጠራው በምን መልክ እንደሚኪያሄድ "ሕዝብ ቆጠራ" በሚባለው ከንቱ ውዳሴ ውስጥ የተሳተፈ ሁሉ ያውቀዋል። እንኳን ለመቁጠር የሚሄደው ቁንጮው የቆጠራ አለቃም ህዝብን በአንደበቱ ለመለያየት ከማገልገሉ ባሻገር የህዝብ ቆጠራን ጠቀሜታ ማወቁን አላህ ይወቀው። የአሳ ግማቱ ከአናቱ እንዲሉ መችም እየፈጠሩ የውሸት ናዳ ሲለቁ መዋል የተጀመረው ከላይ ከተራራው ነውና የቆጠራው ሰነጠረዥ ሁሉ በየቆጠራ ጣቢያው የዛፍ ጥላ ስር የሚሞላው በፈጠራ ነው። ይህ ጸሐፊም ቆጥሮ ወይም ተቆጥሮ ስለሚያውቅ ለዚህ ዋቢ መጥቀስ አያስፈልገውም። እንዲያው ለምናልባቱ  ቅጥፈት ከማይሰለቻቸው ከእነስም- አይጠሩ በስተቀር "አባቴ ይሙት" ሲል ምሎ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር ይህንን ያህል ነው ብሎ ደፍሮ የሚናገር ይኖር ይሆን? ታዲያ የሕዝብ ቁጥር በትክክል የማይታወቅበት፣ የሕዝብ ጤንነትና እድገት አመልካቾች ሥራ ላይ መዋል ቀርቶ የማይታወቁበት የሰው ልጅ መኖሪያ በዚህ ክፍለ-ዘመን ውስጥ አገር ይባላል ወይ?

እስከማውቀው ድረስ በማንኛውም አገር ቋንቋ አገር ሲባል በሕግ የታወቀ ዳር ድንበር ያለው የአለም ክፍል የሆነ መልከአ-ምድር ነው። አዎ የዚህኛውና የዚያኛው አገር ድንበር ይህ ነው ተብሎ በውል መታወቅ ያሻዋል። በመሆኑም በጦቢያም በልጅነታችን ጅኦግራፊ ስንማር ድንበራችን ከዚህ እስከዚህ ነው ይሉን ነበር። እንዲያው በፈጣሪ የዛሬ ጊዜ የጅኦግራፊ አስተማሪዎች የኢትዮጵያ ድንበር ከየት እስከ የት ነው እያሉ  ተማሪዎቻቸውን ያስተምሩ ይሆን? ለእርሱ ምስጋና ይግባው እንኳንም የጅኦግራፊ መምህር ከመሆን አድኖኛል። በጦቢያ የጃኦግራፊ መምህር ብሆንና ይህንን ጥያቄ አስተዋይ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ቢጠይቀኝ የምን አፍ እላፊ ነው ብየ በኩርኩም ከማውለቅ በስተቀር ምን እመልስ ኖሯል? ለመሆኑ የአሁኑን የኢትዮጵያ ድንበር ከዚህ እስከዚህ ነው ብሎ አፉን ሞልቶ የሚናገር ዜጋ አለ? እውነቴን ነው የዛሬው ድንበራችን ከዚህ እስከዚህ ነው ብሎ ደረቱን ነፍቶ መናገር የሚችል እስቲ እጁን መቆስቆሻ አስመስሎ ያውጣ? የነገውን ድንበር ሊተነብይ የሚችል ነቢይ ካለም እስኪ መቁጠሪያውን ይዞ ወደዚህ ይምጣ? ማንም የለም አይደል? ታዲያ ዳር ድንበሩ የማይታወቅ የአለም ክፍል እንዴት ብሎ አገር ይባላል?

አንባቢ ሆይ ችግራችን ጥፍር ብቻ ሳይሆን ስር አውጥቶ እንደ ሽምግልናና ክህነት ካሉት ማህበራዊ ሐብቶቻችን (social institutions) ውስጥ ተንሰራርቶ ማየቱ እንኳን ቡናና ጠላ ሲጃራና ጫትንም ያስከጅላል። ይህን አለ ብላችሁ ግስላ ማቡነን አለዚያም ጀለብያ ለብሳችሁ ጉንጫችሁን በቅጠል መወጠር ብትጀምሩ ግን እኔ የለሁበትም። ውርድ ከራሴ! አንድ አገር አገር ለመሆን በማህበራዊ ኑሮም በእውነት የሚያስታርቁና እውነትን የሚመሰክሩ ሽማግሌዎች፣ ላጠለቁት መስቀል የሚሞቱ ካህናት፣ ሰማይን ካለምሰሶ ላቆመው አላህ ሲሉ መከራን የሚቀምሱ ሸህዎች፣ ምለው በደፉት ዲግሪ የሚገዙ ምሁራን ያስፈልጉታል። "አቡን" ከገዳይ ጎን የሚቆምበት መንበር፣ ጳጳስ ለእግዚአብሔር ቀርቶ የስለት ገንዘብና አስራት እየሞጨለፈ ሆዱን ለሚሞላለት "አቡን" የሚሰግድበት ጽ/ቤት፣ ቀሳውስት የንስሃ ልጆቻቸው በሰበብ አስባቡ በባሩድ ሲጨፈጨፉ ጸሎትና ፍታት የሚከለክሉበት ገዳም አገር ነወይ? ምሁር ነኝ የሚለው ሲመረቅ ያጠለቀውን ቆብ፣ ዳኛው ደግሞ ከችሎት ሲቀመጥ የሚለብሰውን ካባ የነፍሰ ገዳይዎች ደጅ መጥኛ ያደረገበት ችሎት አገር ነወይ? ሽማግሌ ተበዳዩ ጫማ ላይ ይውደቅ፣ ደግሞም በዳዩን ይካስ የሚልበት ዋርካ አገር ነወይ?

በልጅነታችን ስናድግ ምራቃቸውን የዋጡ የሰፈራችን ሰዎች ስለውሸት አደገኛነት ሲያስጠነቅቁን “አትዋሹ! ሰው በውሸት ሲሞላ ባቁላ እንደበዛበት ከረጢጥ ትርትር ይላል” ይሉ ነበር። እውነት ይህ ማስፈራሪያ እውነት ቢሆን ኖሮ ይህ ቤተ-መንግስት የሚባለው ቤተ-ሰይጣን ሲተረተር ውሎ ሲተረተር በሚያድር የባቁላ ከረጢት የቡትቶ ክምር አይሞላም ነበርን? ታዲያ እንግዲህ አገረ-ገዥዎችን ከቅጥፈትና ተንኮል ድርና ማግ የሚሰራ የሸማ መስሪያ የተተከለበት ጉድጓድ አገር ይባላል ወይ? እውነት ከአገር ገዥዎችና ከሃይማኖት መሪዎች እርም አውጥታ የተለየችበት መድረክ አገር ነወይ? ጉድ እኮ ነው! በመዋቀር ከላይ እስከ ታች የቅጥፈት ድንኳን ተከትሮበት ያለ ምድር በምን ቋንቋ ነው አገር ተብሎ የሚጠራው?

ባጠቃላይ ከላይ በተገለጹትና በሌሎችም በዚህ ጽሑፍ ብቻ ተተንትነው በማያልቁ የህብረተሰብ ጠንቆች ተወጥሮ በቋንቋ በቋንቋው ተለይቶ፤ እንደ ቀንድ ከብቶች በበረት ውስጥ ታጉሮ፣ እንደ ጋማ እንሰሶችም በጋጥ ውስጥ ተቀይዶ፣ እንደ በግና ፍየልም ጉረኖ ውስጥ ታስሮ፣ አረመኔ እረኞች ራቁቱን እያስኬዱ የሚግጡት፣ ዛር ሲነሳባቸውም የሚሰውት፣ ካስፈለገም ከሚያርሰው መሬት ጋር የሚሸጡት፣ ጉርሻ ላጎረሳቸው የባእድ መንግስት ሁሉ በስጦታ መልክ የሚያበረክቱት፣ ዳር-ድንበሩን ይህ ነው ብሎ መናገር የማይችል፣ የስሜት ሕዋሳቱ ተቀጥቅጦ እንዳይሰራ የተደረገ፣ በቁሙ የሞተ ሕዝብ ያለበት ምድር አገር ይባላል ወይ? አዎ የአቶ አበበ ጥያቄ “ኢትዮጵያ የማን አገር ናት?” ሲሆን የእኔ የወንድሙ መልስ ደግሞ “ለመሆኑ ኢትዮጵያ አሁን አገር ናት ወይ?” የሚል ጥያቄ ነው። አመሰግናለሁ!

***ዋቢ***


1. *ኢትዮጵያ የማን አገር ናት (አበበ ገላው)* *http://addisvoice.com/amh/ager.pdf* *(accessed 2/8/09)*

2. *ኢትዮጵያዊነት (መስፍን ወ/ማርያም)* *http://www.abbaymedia.com/pdf/Ethiopiawinet.pdf* *(accessed 2/8/09)*

3. *Gray’s Anatomy Edition 2005 (accessed 2/8/09)*

4. *Vital Statistics* *https://www.cdc.gov/nchs/ssbr/023para.htm* *(accessed 2/8/09)*

5. *ጦቢያውያንና ጤንነታቸው* *http://www.abbaymedia.com/pdf/Amharic/Tenna.pdf* *(accessed 2/8/09)*